**“ሠንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጲያ ታላቅ የከፍታ ዘመን ብሥራት፣ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጲያ ሕዳሴ!”**



ሰንደቅ ዓላማ የአንድ አገር ሕዝብ የጋራ መገለጫ ነው። ኢትዮጵያ ዘመን ተሻጋሪ የሰንደቅ አላማ ታሪክ ካላቸው አገራት መካከል አንዷ ስትሆን ሰንደቅ ዓላማውም የአገራችን ሉኣላዊነትና የሕዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት መገለጫ ነው። የኢትዮጵያ ህዝቦች ሰንደቅ አላማን የነፃነታቸውና የሉዓላዊነታቸው ምልክት አድርገው የመረዳት የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላቸው ሲሆን የአገራችን ሰንደቅ ዓላማ ከነጭ የቀኝ አገዛዝ ቀንበር ለመላቀቅ ለታገሉ አፍሪካውያንና መላው ጥቁሮች ሕዝቦችም የነፃነት ኩራት ሆኖ ማገልገሉ እሙን ነው። አገራችን የውጭና የውስጥ ጠላቶች ግንባር ፈጥረው አገራችንን ለማፍረስና ሕዝቦቿን ለመበተን በከፈቱብን ጦርነት መላ ኢትዮጵያውያን ተቀናጅተውና ተናበው መንግስት በጠራው የሕግ ማስከበርና የኅልውና ዘመቻ ላይ በመሳተፍ እና አገር የማፍረስ እብሪታዊ እንቅስቃሴ በመቀልበስ ሰንደቅ ዓላማቸውን ከፍ አድርገው ማውለብለባቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ስለሆነም እኛ ኢትዮጵያውያን የሚያስተሣሥረን ገመድ ሊበጠስ የማይችል ጠንካራ መሆኑን በመገንዘብ ከጊዜያዊ ፈተና ባሻገር ያለውን መጻኢ የጋራ ተስፋችንን በማዬት ዛሬም እንደትላንቱ በተሰለፍንበት የሥራ መስክ እና በቀን ተቀን ሕይወታችን ለሰንደቅ ዓላማችን ክብር እንፋለም ዘንድ ለማስታወስ ብሔራዊ የሰንደቅ አላማ ቀን በኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 3 የተቀመጠውን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ

መንግስት አንቀፅ 3 የተቀመጠውን ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ

ትርጓሜ መሰረት በማድረግ የወጣ ው የሰንደቅ አላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 እንዲሁም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 863/2006 አንቀፅ 2 መሰረት በየዓመቱ ጥቅምት ወር በመጀመሪያው ሳምንት ሰኞ እንዲከበር ተደንግጎል። በዚህም መሰረት በዓሉ ዘንድሮም ለ17ኛ ጊዜ ሰኞ ጥቅምት 3 ቀን 2018 ዓ.ም *“ሠንደቅ ዓላማችን ለኢትዮጲያ ታላቅ የከፍታ ዘመን ብሥራት፣ ለብሔራዊ አንድነታችን፣ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጲያ ሕዳሴ!”*

በሚል መሪ ቃል በመላ አገሪቱ ይከበራል። እኛም በዓሉን በማስመልከት በአዋጁ ከተቀመጠው ቀንጭበን ሥለሰንደቅ ዓለማና ተያያዥ ጉዳዮች ግንዛቤ ሊፈጥር በሚችል መልኩ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፤ መልካም ንባብ!

## የሰንደቅ ዓላማ ምንነትና አገራዊ ትርጉም

**ሰንደቅ:** ማለት ምርኩዝ፣ ምሰሶ በትር፣ ህዝብ ማለት ሲሆን **ዓላማ:** ደግሞ ምልክት፣ የህዝቦች የማንነት መለያ ማለት ነው። ይህም ለሰንደቅ ዓላማ የአንድ አገር መንግስትና ህዝብ ሉዓላዊነት፣ የፖለቲካ ስልጣን ነፃነት፣ እድገትና ማኅበረሰባዊ ትስስር መፍጠሪያ መሣሪያ የሚል ትርጉም ያሰጠዋል። ዜጎች ከሰንደቅ ዓላማው ፊት በቆሙ ቁጥር ልዩ ስሜት ውስጥ የሚገቡት በአገርና በሕዝብ ፊት እንደቆሙ ስለሚቆጥሩ ነው። ሰንደቅ ዓላማ የሕገርና የሕዝብ ያለፈ ታሪክ፣ ወቅታዊ ገፅታና የወደፊት ዓላማ ነፀብራቅም ነው። ለአገርና ለሕዝብ የጠለቀ ፍቅር፣ ክብርና ቁርጠኝነት ያለው ዜጋ ተግባር ልእልና የሚገለጠውም ሰንደቅ ዓላማውን በሰቀለበት ማማ ከፍታ ነው። በተቃራኒው የሰንደቅ ዓላማ መውረድ/መረገጥ የአገርና የሕዝብ ሽንፈት ወይም ውርደት ምልክት ነው። አገራት ከድኅነትና ኋላቀርነት ወጥተው በለውጥ ጎዳና ለመራመድ ሰንደቅ ዓላማቸውን የትግል መሪ፣ የማኅበራዊ ካፒተልና የብሔራዊ ብሄርተኝነት መሰረት አድርገው የሚጠቀሙበትም ለዚህ ነው። ምክንያቱም ሰንደቅ ዓላማ በማንኛውም ደረጃና ሁኔታ ውስጥ የሚኖሩ ሕዝቦች የሁለመናቸው መገለጫ 2

ነው። በአጠቃላይ ሰንደቅ ዓላማ የአንድ አገር ሕዝብና መንግስት ውክልና ያለበት ራሱ አገርና ሕዝብ ማለት ነው።

## ሰንደቅ ዓላማ ብሄራዊ ዓርማና ኢትዮጵያዊ ገጽታ

አሁን ያለው የሰንደቅ ዓላማ ቅርፅና ቀለም ራሱ ረጅም እድሜ ያለው ነው። በየዘመኑ የነበሩ መንግስታት የራሳቸውን ምልክት እያተሙበትም ቢሆን አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማቱን ጠብቆ ብዙ ዘመናትን ቆይቷል። ሶስቱ ቀለማት አንድ ላይ ሳይሰፉና ቅደም ተከተላቸውም እየተዘበራረቀ ጥቅም ላይ ሲውሉም ነበር። የአሁኑ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ አሁን ባለው ቅርፅ ሥራ ላይ የዋለው በ1880ዎቹ መጨረሻ ላይ ነው። ለቀለማቱ የመጀመሪያው ትርጉም የተሰጠውም በ1898 ዓ.ም እንደሆነም ይገለፃል። ባለፉት 150 ዓመታት ውስጥ ሶስቱ ነባር ቀለማት ፀንተው የሰንደቅ ዓላማው ቅርፅም ወጥ ሆኖ በመካከሉ የሚጨመርበት ዓርማ ግን ከመንግስት ለውጥ ጋር እየተለዋወጠ ቆይቷል።

## የኢፌዴሪ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ ዓርማ ሕጋዊ ትርጓሜዎች

የኢፌዴሪ ሕገ-መንግስት አንቀፅ(3) ‹‹የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የአገር፣ የሕዝብ፣ የብኃሀነት፣ የሉአላዊነት፣ የነፃነት፣ የአብሮነት፣ የአስተዋይነት፣ የሕዝባዊነት፣ የሚዛናዊይነት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ማንነት ነው። በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚታየው ብሄራዊ ዓርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ኃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ይሆናል፤” ይላል። የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት የኢፌዴሪ ሰንደቅ ዓላማ ሥርዓትን በዝርዝር ያቋቋመ ሕግ በአዋጅ ቁጥር 654 /2001 ዓ.ም አውጥቷል። በዚሁ አዋጅ ድንጋጌ

1. ሰንደቅ ዓላማው የሪፐብሊኩ ሉዓላዊይነትና የኢትዮጵያ ብሄሮች ፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በፍላጎትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነታቸው መገለጫ ምልክታቸው ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል፤ አንቀፅ(5)፤

2. ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ ፣ ከመሀል ቢጫ ከታች ቀይ ሆኖ በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ የተቀረፀ ብሄራዊ አርማ ይኖረዋል፡፡ አርማው በሰንደቅ ዓላማው መካከል ላይ የሚያርፈው የክቡ ዙሪያ የአረንጓዴውንና የቀዩን ቀለም ቁመት አጋማሽ አካል ይሆናል አንቀፅ6(1)፡፡ የሰንደቅ አላማው ቀለማቱ ብሩህና መሰረታዊ ናቸው(አንቀፅ6(1)፤ እነዚህ ቀለማት አግድም የተዋቀሩና እኩል ስፋት የሚኖራቸው ሆኖ የሰንደቅ ዓላማው ወርድ የቁመቱን ዕጥፍ ይሆናል አንቀፅ6(2)፡፡

3. ሰንደቅ ዓላማው ላይ ተቀርፆ የሚቀመጠው የብሄራዊ አርማው ቅርፅ ክብ በሆነ ሰማያዊ መደብ ላይ ሆኖ በየአቅጣጫው መጥተው የሚገናኙ ቀጥታና እኩል ቢጫ መስመሮች ይኖሩታል(አንቀፅ 6/4/ሀ)፡፡ ሰንደቅ ዓላማው ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረ ኮከብ የሚኖረው (አንቀፅ6/4/ሀ) ሲሆን ቀጥታና እኩል በሆኑ መስመሮች መተላለፊያ ላይ የሚፈነጠቅ ቢጫ ጨረር ይኖረዋል፡፡

## <u>የሰንደቅ ዓላማ ቀለማት ትርጓሜ</u>

አረንጓዴው የስራ ፣ የልምላሜና የዕድገት ምልክት (አንቀፅ 7/1/)፣ ቢጫው የተስፋ ፣የፍትህና የእኩልነት ምልክት (አንቀፅ 7/2/) ቀዩ ለነፃነትና ለዕኩልነት መስፈን የሚደረግ የምስዋትነትና የጀግንነት ምልክት(አንቀፅ7/3) **ነው፡፡** **<u>የኢፌዴሪ ብሔራዊ ዓርማ ትርጉም</u>**

1. ክብ የሆነው ሰማያዊ መደብ ላይ (አንቀፅ8(1) ቀጥታና እኩል የሆኑት መስመሮች የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እንዲሁም የኃይማኖቶች

2. ቀጥታና እኩል ከሆኑ መስመሮች ፡ የተዋቀረው ኮከብ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰበቦችና ህዝቦች በመፈቃቀድ የመሰረቱት አንድነት እና ቢጫ ጨረር በመፈቃቀድ አንድነት ለመሰረቱት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የፈነጠቀውን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል፡፡ (አንቀፅ8/3/) የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የሀገር ፣ የህዝብ፣ የብዝሀነት ፣ የሉአላዊይነት ፣የነፃነት ፣ የአብሮነት፣ የአስተዋይነት ፣ የህዝባዊይነት ፣ የሚዛናዊይነት በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ማንነት ነው፡፡ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የሚታየው ብሄራዊ አርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ኃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ይህም ማለት ብሔራዊ ዓርማው የብዝኃነት፣ የዲሞክራሲያዊ አንድነትና የሕዳሴ ማገር ሆኖ የኢትዮጵያን ህዝቦች እንደ ብረት የጠነከረ ማህበራዊ ካፒታል እየገነባ የሚጓዝ ማህተም ነው፡፡

## <u>በኢፌዴሪ የሰንደቅ ዓላማ ሥርዓት የተከለከሉና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት (23)</u>

ብሔራዊ ዓርማ እንዲኖረው የሚያዘውን ሰንደቅ ዓላማ ዓርማውን ሳያካትቱ መጠቀም፣ በሰንደቅ ዓላማው ላይ ባዕድ ምልክት ማሳረፍ፣ ከዕድሜ ብዛት የተነሳ ለአገልግሎት ብቁ ያልሆኑ በእርጅናም ይሁን በልዩ ልዩ ምክንያት የሰንደቅ ዓላማው ቀለም በህጉ ከተፈቀደው የብሩህነት ደረጃ በወረደ መንገድ መጠቀም፣ በሰንደቅ ምሰሶ ላይ ማስታወቂያ መለጠፍና ያላአግባብ ሌሎች ሰንደቅ ዓላማዎችን ወይም ዓርማዎችን ጨምሮ ማውለብለብ ወይም መገልገል፣ ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ሰንደቅ ዓላማውን በጽሁፍ ወይም በቃላት ወይም እንዲሁም የብሄራዊ ዓርማውን መጠን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገል የሕግ ተጠያቂነትን የሚያስከትሉ ተግባራት ናቸው፡፡

## የወንጀል ቅጣቶች(24)

1. ሰንደቅ ዓላማው ላይ ቃላቶችን መፃፍ ወይም ሌላ ባዕድ የሆኑ ነገሮችን ጨምሮ መገልገል፣ የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት ቅደም ተከተል እንዲሁም የብሄራዊ ዓርማውን መጠን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገልና ሌሎችን ጥፋቶች የፈፀመ እስከ ብር 3000(ሶስት ሽህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት የሚደርስ ፅኑ ዕስራት የሚያስቀጣ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

2. ሰንደቅ ዓላማውን በህግ በተደነገገው መሰረት ብሄራዊ ዓርማውን ሳያካትቱ መጠቀም እስከ ብር 5000 ( አምስት ሽህ ብር ) በሚደርስ የገንዘብ መዋጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት ከስድስት ወር በሚደርስ ፅኑ ዕስራት ይቀጣል ሲል ይደነግጋል፡፡ ብሔራዊ ዓርማውን ሳያካትት የተጠቀመው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል የሆነ እንደሆነ የገንዘብ ቅጣቱ ሁለት እጥፍ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡

በመሆኑም 15ኛው የሰንደቅ ዓላማ ስናከብር ኢትዮጵያ አገራችን አሁን ካለችበት የሰላም እጦትና አለመረጋጋት ችግሮቿ ወጥታ ሕዝቦቿ በነፃነት፣ በመከባበርና በመዋደድ የሚኖሩባት አገር እንድትሆን የበኩላችንን አገራዊ ግዴታ በመወጣት ሊሆን ይገባል፡፡ በተጨማሪም ጥያቄዎችና ልዩነቶች እንከኳ ቢኖሩን በሕገ-መንግስቱም ሆነ በአዋጆች እውቅና ያገኘውን ሰንደቅ ዓላማ ማክበርና ማስከበር እንዲሁም በጋራ ከፍ አድርጎ ማውለብለብ ከሁላችን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና
ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈፃሚ

ጥቅምት 2018 ዓ.ም